የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት
ልሣነ- ሕግ ጋዜጣ
LISAN HIG GAZETA
OF THE BENISHANGUL — GUMUZ REGIONAL STATE
የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት
ም/ቤት ጠባቂነት የወጣ

18ኛ ዓመት አዋጅ
ቁጥር 104 ጥር 2004
አሶሳ

# አዋጅ ቁጥር 104/2004 ዓ/ም

## የተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳዳርን ለማጠናከር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 86/2002 እንደገና ለማረም የወጣ አዋጅ

### መግቢያ

በተሻሻለው በክልሉ ህገ መንግስት እና በዚህ አዋጅ መሰረት ለአካባቢ አስተዳዳሮች የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ህጋዊ አሰራርን ተከትሎ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑና፣

በተለይም ለወረዳና ለቀበሌ አስተዳዳሮች እንዲሁም ለመንግስት አካላት በህገ መንግስቱ የተሰጣቸውን ስልጣንና ኃላፊነት በተገቢው እንዲወጡ ለማስቻልና ለዚህም የህግ ማዕቀፍ መኖሩ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

በዚህ መሠረት የክልሉ መንግስት ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 49 (3፣1) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፣

### አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣውን አዋጅ እንደገና ለማረም የወጣ አዋጅ ቁጥር 104/2004 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### አንቀጽ 2 ማሻሻያ

የተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አካበቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣ አወጅ ቁጥር 86/2002 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) የተጠቀሰውና አምስት ሽህ የሚለው እንደሚከተለው ታርሟል።

በዚህ መሠረት አዋጅ ቁጥር 86/2002 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) ላይ የተጠቀሰውና አምስት ሽህ የህዝብ ብዛት የሚለው 50,000 /ሃምሳ ሽህ/ በላይ የህዝብ ብዛት በሚለው ታርሟል።

### አንቀጽ 3

ይህ አዋጅ በክልሉ ልሳነ ህግ ጋዜጣ ታተሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አሶሳ

ጥር 30/2004 ዓ/ም

አህመድ ናስር አህመድ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዚዳንት